# አማሌቅ ይሸነፍ

በመጋቢ አስቻለው በየነ

## ክፍል አንድ

በዚህ በያዝነው ዓመት እ.ኤ.አ. 2007፣ እግዚአብሔር አማሌቅን የምናሸንፍበትን ሃይልና ጉልበት ሊያጎናፅፈን አልፎም የራሱን መለኮታዊ የውጊያ ስልት ሊሰጠን ይፈልጋል:: መንደርደሪያ እንዲሆነን የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወስደን በመመልከት እግዚአብሔር ሊናገረን የሚፈልገውን መልዕክት እንረዳ::

*«አማሌቃውያን መጥተው እስራኤላውያንን ራፊዲም ላይ ወጉ ሙሴም ኢያሱን ከሰዎቻችን አንዳንዶቹን ምረጥና አማሌቃውያንን ለመውጋት ውጣ:: በነገው እለት የእግዚአብሔርን (ኤሎሂም) በትር በእጆቼ ይዤ በኮረብታው ጫፍ ላይ እቆማለሁ::ስለዚህ ኢያሱ ሙሴ ባዘዘው መሰረት ከአማሌቃውያን ጋር ተዋጋ ሙሴ አሮንና ሖርም ወደ ኮረብታው ጫፍ ወጡ:: ሙሴ እጆቹን ወደ ላይ በሚያነሳበት ጊዜ ሁሉ እስራኤላውያን ድል ያደርጉ ነበር:: እጆቹን ባወረደ ጊዜ አማሌቃውያን ያሸንፉ ነበር:: የሙሴ እጆች እየዛሉ በሄዱ ጊዜ ድንጋይ ወስደው ከበታቹ አደረጉ እርሱም ተቀመጠበት አሮንና ሖርም አንዱ በአንዱ በኩል ሌላው በሌላ በኩል ሆነው እጆቹን ወደ ላይ ያዙ:: ይኸውም እጆቹ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ጸንተው እንዲቆዩ ነው:: ስለዚህ ኢያሱ የአማሌቃውያንን ሰራዊት በሰይፍ ድል አደረገ:: ከዚያም እግዚአብሔር (ያህዌ) ሙሴን «ሲታወስ እንዲኖር ይህን በጥቅልል መጽሐፍ ላይ ጻፈው ኢያሱም መስማቱን አረጋግጥ ምክንያቱም የአማሌቃውያንን ዝክር ከሰማይ በታች ፈፅሜ እደመስሳለሁ»አለው::ሙሴም መሠዊያውን ሰርቶ «እግዚአብሔር (ያህዌ) አርማዬ ነው» ብሎ ሰየመው:: «እጆች ወደ እግዚአብሔር (ያህዌ) ዙፋን ተዘርግተዋልና እግዚአብሔር (ያህዌ) አማሌቃውያንን ከትውልድ እስከ ትውልድ ይዋጋቸዋል» አለ::* **ዘጸ.17፥8-15**

## 1) ውጊያው መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አይደለም!

የዚህ ነገር ቁልፍ ምስጢር ያልገባው አማኝ በዚህ ምድር ላይ የድልን ሕይወት ለመኖር አይችልም:: ስለዚህ ጠላት ይህንን ስለሚያውቅ የብዙ ክርስቲያኖችን የጸሎት ሕይወት የቀማው በተለያዩ ነገሮች ተጠምደው እንዲባክኑ በማድረግ ነው! ቀደም ብለን ባነበብነው ክፍል ውስጥ የምንገነዘበው ነገር እስራኤል ባለ ድል የሆነው ኢያሱ ስለተዋጋ ብቻ ሳይሆን ሙሴም በተራራ ላይ ሆኖ እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ስላነሳ ነበር::

የሙሴ እጆች ሲበረቱ ኢያሱ ይበረታል የሙሴ እጆች ሲደክሙ ደግሞ የኢያሱም ይደክማል ስለዚህ የሙሴ እጆች ወደ ላይ ካልተነሱና ካልበረቱ የኢያሱ እጆች ብቻቸውን ምንም ማድረግ አይችሉም ማለት ነው:: ሙሴና ኢያሱ አንድ ቦታ ላይ ቆመው አልተዋጉም ምንም እንኳ በሚታይ ቦታ የቆመው ኢያሱ ቢሆንም ወይም በዓይን ከሚታይ ጠላት ጋር የተዋጋውና የተጋፈጠው ኢያሱ ቢሆንም የሙሴ ሥፍራ ግን በጠላት ፊት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ነበር:: ድል ለእስራኤል የመጣው በእግዚአብሔር ፊት ከቆመው ከሙሴ እንጂ በጠላት ፊት ከቆመው ከኢያሱ አልነበረም::

ስለሆነም የዚህ ነገር ምስጢር ከገባን ቶሎ ብለን ወደ ትክክለኛው ስፍራችን መመለስ ይኖርብናል ምክንያቱም ወደ ተራራው ስንወጣ ወይንም ወደ ፀሎት ሥፍራ ስንመለስ ጠላት ይሸነፋል:: ድል ያለው በተራራ ላይ እንጂ በሜዳ ላይ አይደለምና!

*ወደ ተራራው ስንወጣ ወይንም ወደ ፀሎት ሥፍራ ስንመለስ ጠላት ይሸነፋል:: ድል ያለው በተራራ ላይ እንጂ በሜዳ ላይ አይደለምና!*

## 2) የእግዚአብሔር በትር

ሙሴ ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ ባዶ እጁን ሳይሆን የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ነበር የወጣው:: የእግዚአብሔር በትር ሲል ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ነገር ይዞ መውጣቱን ያሳያል:: አማኝ የሚዋጋው የእግዚአብሔርን ነገር ይዞ እንጂ የራሱን ነገር ይዞ አይደለም:: ጠላታችንንም የምናሸንፈው በእግዚአብሔር ነገር እንጂ በሰው ነገር አይደለም::

የብዙዎቻችን መንፈሳዊ ሕይወት ቢመረመርና ቢታይ እርግጠኛ ነኝ ብዙዎቻችንን ጠላት የእግዚአብሔርን ነገር አስጥሎናል የሚል ግበት አለኝ:: እስኪ በዚህ ዓመት ቆም እንበልና ወደ ኋላችን እንመልከት ምንድነው የጣልነው? ወይንስ የያዝነው? ምናልባት መጣል የሚገባንን ይዘን፣ መያዝ የሚገባንን ግን ጥለን እንዳይሆን!

የዚህ ዓለም ሩጫና የኑሮ ጫና ከፀሎት ሥፍራችን አስለቅቆን እንደሆን ወደ ሥፍራችን እንመቀስ:: ምክንያቱም እስራኤል አማሌቅን ያሸነፈው በሙሴ ፀሎት እንጂ በኢያሱ የውጊያ ብቃት አልነበረም:: የድል አድራጊነቱ ቦታ የሙሴ እንጂ የኢያሱ ቦታ አልነበረም:: ብዙዎቻችን ከብዙ ነገር ጋር እየተዋጋን ነገር ግን በሕይወታችን ድልን መጎናፀፍ ያቃተን በትክክለኛ ቦታ ላይ ባለመቆማችን ነው:: በዚሁ አንፃር የጣልነውስ ነገር ምንድነው? አሁንም የኑሮ ነገር በጣም ስለያዘንና ጊዜአችንን ስለሚወስድብን በብዙዎቻችን ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ሥፍራ አጥቷል:: በስንት የክርስቲያኖች ቤት ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚገባ እንደሚነበብ ባላውቅም ዛሬ ግን የብዙዎች ሕይወት መርከብ ያለ መሪ ሆኖ የቀረው በዚሁ ምክንያት ነው::

መዝሙረኛው ሲናገር «*ሕግህ ለመንገዴ ብርሃን ለእግሬ መብራት ነው:*» ሲል እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚኖር አማኝ በብርሃን እንደሚኖር አረጋግጦ ይነግረናል ይሁን እንጂ ብዙ ክርስቲያኖች ለቃሉ ጊዜና ቦታ ስላልሰጡት ሕይወታቸው በጨለማ እንደሚደናቀፍ ሰው መስሏል:: ስለዚህ ሕይወታችንን አጥብቀን እንመርምር ለእግዚአብሔር ቃል መስጠት የሚገባው ጊዜ በሌላ ነገር ተተክቶ ከሆነ በዚህ በያዝነው ዓመት የጌታ ቃል በቦታው ይመለስ:: እነዚህን ነገሮች በፍጥነት ካላስተካከልን ሕይወታችን መቼውንም ቢሆን ሊስተካከል አይችልም::

## 3) *መደጋገፍ*

ሙሴና ኢያሱ የቆሙት ለየብቻቸው ሳይሆን ከሌሎችም ጋራ ነበር:: ስንጠራ ለብቻችን እንዳልተጠራን ሁሉ ብቻችንንም መቆም አንችልም:: ብቻውን የሚቆምነ ብቻውንም የሚዋጋ ኖብቻውን የሚያሸንፍ....ሰው የለም:: እግዚአብሔር አንድን ሰው ለአንድ ጉዳይና ለተወሰነ ሥራ ሲጠራው ኖ ከእርሱም ጋር አብረው የሚቆሙትን ሰዎች አብሮ ያስነሳለታል::

ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን በትር በእጁ የያዘው ሰው ሙሴ ቢሆንም ወደ ተራራው በወጣ ጊዜ ግን አብረውት የሚቆሙትን ሁለት ሰዎች ጨበሮ ይዞ ወጣ:: የእግዚአብሔርን ነገር የያዝነው እኛ ብንሆንም ራዕያችን ግን የግድ በሌሎችም መደገፍ ይኖርበታል:: ድጋፍ መስጠት ቀላል አገልግሎት ሊመስለን ይችላል ኖ ነገር ግን ሁለቱ ሰዎች ለእግዚአብሔር ሰው ለሙሴ ድጋፍ ሆነው ባያቆሙት ኖሮ እስራኤል ይሸነፍ ነበር::

በዚህ ጦርነት የአራት ሰዎች እጅ ይታያል እነዚህም በሁለት እጆች የተደገፉት የሙሴ እጆች ነበሩ! የኢያሱ እጅ ግን የተደገፈው በሙሴ እጅ ነበር:: ኢያሱና ሙሴ ምንም እንኳ አጠገብ ላጠገብ ባይሆኑም ነገር ግን ሙሴ እጁን በሚያነሳበት ጊዜ ኢያሱ ሲያሸንፍ እጆቹን ሲያወርድ ደግሞ ኢያሱ ይሸነፍ ነበር:: ስለዚህ በመንፈሳዊው ዓለም የሁለቱም እጆች ተያይዘዋል ማለት እንችላለን!

> ***ብቻውን የሚቆም፣ ብቻውንም የሚዋጋ ፣ብቻውን የሚያሸንፍ....ሰው የለም::***

## 4) የሙሴ እጅ

ምንም እንኳን አማሌቅን በሜዳ ላይ የተጋፈጠው ኢያሱ ቢሆንምነ ለእስራኤል መሸነፍና ማሸነፍ ወሳኝ የነበረው የሙሴ እጅ እንጂ የኢያሱ አልነበረም:: ይህ ለምን ሆነ ቢባል የእግዚአብዘሔር በትር የነበረው በሙሴ እጅ ላይ እንጂ በኢያሱ እጅ ላይ ስላልነበረ ነው:: በሌላ አባባል ኢያሱንም ጨበሮ ሁሉም ደግፈው የያዙት  የሙሴን እጅ ነበር ኖ ምክንያቱም ጠላት የሚሸነፍበት በትር የነበረው በሙሴ እጅ ላይ ስለሆነ ነበር::

**ይቀጥላል...**

# በመጨረሻም እነዚህን ሦስት ነገሮች እንመልከት

## 1. የት ነው የቆምነው?

በአማሌቅ ላይ ድልን የምናገኘው በእግዚአብሔር ፊት ስንቆም ብቻ ነው። እስራኤል ድልን ያገኘው በተራራ ላይ በቆመው በሙሴ ነበር ሙሴ በተራራ ላይ ሲቆም ኢያሱ ምርኮን ይማርካል። አንተ በእግዚአብሔር ፊት ከቆምክ ጠላት በፊትህ ሊቆም አይችልም።ተራራ የፀሎት ሥፍራ እንደዚሁም ፣ የጦርነት ሜዳ ነውና ፣ንፈሳዊ ጦርነት የሚካሄደው በሥጋ ሃይልና ጉልበት (በሰው ጥበብ) ሳይሆን ጠላት የሚሸነፈው በፀሎት ነው ምክንያቱም ምንም እንኳን በሚታይ ዓለም ውስጥ ብንኖርም ጦርነቱ ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም። የሚዋጉን በዓይን የሚታዩት ሳይሆኑ የማይታዩት ናቸው። ኤፌ.6÷12-18 *«....ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ከሥልጣናትና ከሃይላት እንዲሁም ከሰማያዊ ሥፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው። ክፉው ቀን ሲመጣ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ፤ ሁሉን ከፈጸማችሁ በኋላ ጸንታችሁ መቆም ትችላላችሁና። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ዝናር ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣በሰላም ወንጌል ዝግጁነት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ። ከእነዚህም ሁሉ ጋር፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላፃዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሱ፤ የመዳንን ራስ ቁር አድርጉ፤ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመና ሁሉ ፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ።»* ጦርነቱን የተዋጋው እና ያሸነፈው የጸሎት ሰው የሆነው ሙሴ ነበር ያሸነፈው የጸሎት ሰው ሙሴ ነው። ኢያሱ ግን ምርኮን ነበር የሰበሰበው።

ብዙ ክርስቲያኖች ምርኮን ለመማረክ በሥጋ ብዙ ይደክማሉ፣ ይለፋሉ ነገር ግን አይሆንላቸውም። ከእንግዲህ በኋላ በሕይወታችን ውስጥ ያሉትንና የሰለጠኑብንን አማሌቃውያንን ለማሸነፍ የራሳችንን መንገድ ትተን እግዚአብሔር ራሱ የሚያሳየንን የራሱን መለኮታዊ ምሪትና የውጊያ ስልት እንድንከተል ያስፈልጋል።

ሀ. የመንፈሳዊ ውጊያ ምስጢር ያልገባውና ውጊያ ምን እንደሆነ የማያውቅ ክርስቲያን ምርኮን ሊማርክ አይችልም። ያልተዋጋ ክርስቲያን እንዴት ምርኮን ይማርካል? ብዙዎቻችን የቆምነው ኢያሱ በቆመበት ቦታ ነው። ጠላት የተሸነፈው በኢያሱ ጉልበት ሳይሆን በሙሴ ጉልበት ነበር። በራሳችን ሃይል ፣ በራሳችን ጉልበትና ፣ በራሳችን ጥበብ ተዋግተን ልናሸንፍ አንችልም። ብዙዎቻችን ውጊያውን እየተዋጋን ነው ግን ማሸነፍ ነው ያቃተን ጠላት በሥጋና በደም እንደማይሸነፍ ስለሚያውቅ እኛ ስንለፋና ስንደክም እርሱ ግን ደስ ይለዋል። እንዳንጸልይና እንዳንበረከክ ፣ እንደ ሙሴም ወደ ተራራው እንዳንወጣ ጊዜአችንንና ዘመናችንን ጠላት በተለያየ ነገሮች ይዞብናል። **በ2007** ግን ጠላት የያዘብንን ነገር እናስለቅቅ፣ ወደ ጸሎት ተራራም እንውጣ ፣ የእስራኤልን ጦርነት የተዋጉትና አማሌቅን ያሸነፉት በተራራ ላይ የቆሙት እነ ሙሴ ነበሩ። **በ2007** እስቲ ወደ ተራራው እንውጣ።

ወደ ተራራ የሚወጡ ሰዎች በስውር ሥፍራ ላይ ስላሉ ማንም በቀላሉ አያያቸውም። አማሌቃውያን ፊት ለፊት የተጋጠሙት ከሙሴ ጋር ሳይሆን ከኢያሱ ጋር ነበር። ለሙሴ እውነተኛው ተጋድሎ (ጦርነት) በሚታየው ሳይሆን በማይታየው ዓለም መሆኑን ተገንዝቧል። በሚታየው ላይ የሚሰለጥነውና የሚሰራው የማይታየው ነው። ብዙውን ጊዜ ሰይጣን በሰዎች ተጠቅሞ እኛ በሰዎች ላይ ቂም እንድንይዝና እርስ በርሳችን እንድንናከስ ያደርጋል። ሃዋርያው ግን ሲናገር «በሰይጣን እንዳንታለል የእርሱን ሃሳብ አንስትምና » ይላልና። ዲያብሎስ እርሱ ራሱ በሚሰራው ሥራ እርሱን እንድናውቅና እርሱን ለይተን እንድናይ አይፈልግም ምክንያቱም እርሱን ካወቅነውና ካየነው ሰዎችን ትተን ተጋድሎአችንን ከእርሱ ጋር እንደምንጀምር ስለሚያውቅ ነው ምክንያቱም ይህ ከሆነ ጠላት ይሸነፋልና ታዲያ ይህ እንዳይሆን ግን ብዙዎችን በማታለል ሥራው አሳምኗቸዋል። የእርሱን ሃሳብ በሰዎች ውስጥ ካየንና ከተረዳን ሰዎቹን ትተን መንፈሱን መገሰጽና ማሰር እንችላለን። ይህ ደግሞ ለአማኝ የተሰጠ ሥልጣን ስለሆነ ሰይጣን ምርጫ የለውም። አሁንም ቢሆን አማኞች ደግመን ደጋግመን ማወቅና ማየት የሚገባን ነገር ቢኖር እውነተኛ ጦርነት ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው። *«የምንኖረው በዚህ ዓለም ቢሆንም የምንዋጋው በዚህ ዓለም ስልት አይደለም። ደግሞም የምንዋጋበት የጦር መሣሪያ የዚህ ዓለም መሣሪያ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ምሽግን ለመደምሰስ የሚችል መለኮታዊ ሃይል ያለው ነው። በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሳውን ክርክርና ከንቱ ሃሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን። መታዘዛችሁ በተፈጸመ ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ለመቅጣት ተዘጋጅተናል።»2ቆሮ.10÷3-6*

**በ2007** ዓይናችን እንዲገለጥና የጠላትን ነገር አጥርተን እንድናይ እግዚአብሔር የመገለጥን መንፈስ ሊሰጠን ይፈልጋል። ስለጠላት በምናስብበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዲኖረን ያስፈልጋል። አእምሮአችን ካልተቀየረ ሕይወታችን ሊቀየር አይችልም! የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር «ሰው በልቡ እንደሚያስበው ነው » ይላል። የምንዋጋው ጦርነት መንፈሳዊ መሆኑን ካወቅንና ከተረዳን በሥጋ የመድከም ነገር ከ2006 በኋላ ይብቃ ምክንያቱም በሥጋ በደከምንባቸው ዓመታት በሙሉ ምንም ፍሬ ስላላፈራን አሁንም እንደዛው እንቀጥል ብንል ዓመቱ ይቀየራል እንጂ ሕይወታችን አይቀየርም። ስለዚህ በዚህ ዓለም ሳለን የድልን ሕይወት ተጎናፅፈን እንድንኖር ካስፈለገ በሕይወታችን መቅደም ያቀበት ነገር ምን እንደሆን ማወቅ ይኖርብናል። ከእንግዲህ በኋላ ሕይወታችን የሚቀየረው በገባን ነገር ስንኖርና ነገሮችን እንደገና ቅደም ተከተል ስናስይዝ ብቻ ይሆናል።

## 2. በእጃችን ውስጥ የያዝነው ነገር ምንድነው?

ሙሴ የራሱን በትር በኮሬብ ተራራ ላይ ጣለ የእግዚአብሔርን በትር ግን ይዞ ወደ ግብፅ ተመለሰ ይህን በማድረጉ ፈርኦን ሊቋቋመው አልቻለም:: አሁንም **በ2007** አማሌቅን ለመቋቋምና ለማሸነፍ የራሳችንን ነገር እንጣልና የእግዚአብሔርን ነገር እናንሳ:: አማሌቅ በእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር በእኛ አይሸነፍም:: *«ፈረስ ለጦርነት ቀን ይዘጋጃል ድል ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው::»ምሳ.21÷31* ሙሴ በምድረበዳ ውስጥ እያለ የተጠቀመበት በትር የእረኝነት በትር ነበረች:: ሆኖም ግን እግዚአብሔር በኮሬብ ተራራ ላይ የራሱን በትር አስጥሎታል:: ወደ ግብፅ ግን ሲመለስ የያዘው በትር የሙሴ በትር ሳይሆን የእግዚአብሔር በትር ነበረች:: እንደ እኔ እምነት ሙሴ እግዚአብሔርን «እኔ ይሄንን ሥራ ማከናወን አልችልም» ባለው ጊዜ እግዚአብሔር ግን <u>«የራስህን በትር ይዘህ አትችልም ከእንግዲህ በኋላ</u> <u>ግን የእኔን በትር ስለምትይዝ የእኔን ሥራ ልትሰራ ትችላለህ</u>» ያለው ይመስለኛል::የእግዚአብሔር በትር የተዓምራት በትር ናትና:: ዛሬም የእግዚአብሔርን ጦርነት ለመዋጋት የእግዚአብሔርን ነገር ማንሳት ይኖርብናል:: የሙሴ እጅ ለእስራኤል እንደ እግዚአብሔር እጅ ነበር ፣እግዚአብሔር ለእስራኤል በዚህ እጅ ተዋጋ ፣ በዚህ እጅ ለእስራኤል ድልን ሰጠ ፣ በዚህ እጅ አማሌቅን አሸነፈ ፣ በዚህ እጅ ባህሩን ከፈለ እንደዚሁም ውሃን ከድንጋይ አፈለቀ......ወዘተ:: ዛሬም እኛ የእግዚአብሔር እጅ በመካከላችን እንዲገለጥ ሁልጊዜም እንጸልያለን እግዚአብሔር ግን <u>«የሙሴ እጆች እጆቹ ናቸውና እርሱን</u> <u>ብትደግፉት ይሆንላችኋል ነው»</u> የሚለን:: እግዚአብሔር የሚለው «<u>ሌላ እጅ አትጠብቁ የናንተ እጆች እጆቼ ናቸው እኔ ሌላ እጅ የለኝም!</u>» ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠንን ነገር ካልያዝን ይሄ ሊሆንልን አይችልም::

## 3. *መያያዝ መደጋገፍና አንድ ሆኖ መቆም*

ውጊያው የአንድ ሰው ውጊያ አይደለም በቁጥር ብዙ ብንሆንም ነገር ግን የምንቆመውና የምንዋጋው እንደ አንደ ሰው ሆነን ነው:: እግዚአብሔር ለእስራኤል ድልን የሰጠው በሙሴ በአንድ ሰው እጅ ሲሆን በሙሴ ነገር ግን የደገፉት ሰዎች ሁሉ የቆሙት እንደ አንድ ሰው ሆነውና አንድ እጅ ይዘው ነበር:: ሁላችንም የየራሳችንን ነገር መያዝ ትተን የእግዚአብሔርን ነገር ብቻ ይዘንና ደግፈን እንቁም::

## 4. የእግዚአብሔር ተራራ

*ሀ.* <u>*የኮሬብ ተራራ*</u> (የእግዚአብሔር ተራራ) በዚህ ተራራ ላይ የሆነውን እንመልከት:-

- ሙሴ የራሱን የእረኝነት በትር ጥሎ የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲከናወን የምታስችለውን በትር ያነሳበት ቦታ ነው::
- ለእስራኤል ሕዝብ ከእግዚአብሔር ራዕይንና ተልእኮን የተቀበለበት ተራራ ነው:: ሙሴ ወደዚህ በወጣባቸው ጊዜያት ሁሉ ከአንድ ሰው ጋር ብቻ ነበር:: ይህም ሰው እግዚአብሔር ነበር:: ወደ እግዚአብሔር ተራራ የሚወጡ፣ እግዚአብሔርን የሚያነጋግሩ የእግዚአብሔር ነገር ያለባቸውና የሚታይባቸው ባለ ራዕይ መሪዎች ያስፈልጉናል::

<u>ለ. የሲና ተራራ:-</u> እንደዚሁም ሙሴ በሲና ተራራ ላይም ብቻውን ከእግዚአብሔር ጋር ነበር:: መቼውም ቢሆን ሙሴ ወደ ተራራ ሲወጣ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ነገር ነበር:: እግዚአብሔር ወደ ተራራው እንድንወጣ ወደ እርሱ እንድንቀርብ ፣ ከእርሱ ጋር እንድንነጋገርና ፣ ከእርሱ እንድንቀበል ይጠራናል:: በእግዚአብሄር ልብ ውስጥ የነበረችውን የመገናኛውን ድንኳን አጣጣል ሙሴ የተቀበለው በተራራ ላይ ነበር:: ሙሴ ከተራራ ላይ ሲወርድ ባዶ እጁን ሳይሆን ለእስራኤል ሕዝብ መልዕክትና ራዕይን ይዞ ይመጣ ነበር:: እግዚአብሔርን የሚያውቁ ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩ የእግዚአብሔር ነገር ያለባቸው መሪዎች ዛሬም ይብዙልን::እንደዚሁም ሁሉ ሙሴ አስርቱንም ትዕዛዝ የተቀበለው በተራራ ላይ ነበር:: **በ2007** ወደ እግዚአብሔር ተራራ እንውጣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ነገር እንቀበል::

<u>ሐ.</u> በዘጸአት 17 ላይ ሙሴ የወጣበትን ተራራ የምልጃ ተራራ ብዬዋለሁኝ:: እግዚአብሔር በዚህ ተራራ ላይ ሙሴን ስላየ ኢያሱን አሰበው::

***መ. ማቴዎስ 17÷1*** *«ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ፣ጴጥሮስንና ያዕቆብን እንዲሁም የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን ወደ አንድ ከፍ ያለ ተራራ ብቻቸውን ይዞአቸው ወጣ::በዚያም በፊታቸው መልኩ ተቀየረ፣ ፊቱ እንደ ፀሐይ አበራ፣ ልብሱም እንደ ብርሃን አንጸባረቀ:: ወዲያውም ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው::»* በአዲስ ኪዳንም ሙሴ በተራራ ላይ ታይቷል እዚህ ተራራ ላይ ለብቻው አልነበረም ከኤልያስ ጋር ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር:: ተራራ ለሙሴ ምንድነው ብትሉ እግዚአብሔርን ለብቻው የሚያነጋግርበት ቦታ ነው:: **በ2007** እግዚአብሔር የሚለን ነገር ተለዩ ወደ ተራራዬም እያለን ነው:: ሙሴ ከሕዝቡ እየተለየ ለብቻው በተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገር ነበር:: ወደ እግዚአብሔር ተራራ እንውጣ እግዚአብሔር የግል አምላክ ነውና በግላችን እንየው ፣እንወቀው ፣ እናነጋግረው::

# እግዚአብሔርን በቤትህ ታውቀዋለህ?

በብዙዎች ቤት ውስጥ እኔ የለሁኝም ብዙዎች በቤታቸው አያመልኩኝም፣ ቃሌ አይነበብም በቤታቸው አላውቃቸውም በጓዳቸው ውስጥ አላውቃቸውም:: በአደባባይ ያመልኩኛል በቤታቸው ውስጥ ግን ረስተውኛል:: እግዚአብሔር በቤታችሁ ውስጥ እንድታመልኩት ፣ በእልፍኞቻችሁ ውስጥ እንድታነጋግሩት ፣ ወደ ማደሪያችሁ ሊመጣ ይፈለጋል ፣ ክብሩ ወደ ቤታችሁ ሊመጣና በጓዳችሁ ውስጥ ይገለጥ ዘንድ ይፈልጋል:: ጌታ ሲናገር *ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ በስሜ ...... »* እኔ በመካከላችሁ ነኝ ይላል:: ባልና ሚስት ሁለት ሆናችሁ በቤታችሁ ውስጥ ብታመልኩት እግዚአብሔር በቤታችሁ ውስጥ ሊገለጥ ይፈልጋል::

**በ2007** እግዚአብሔር ወደ ቦታችሁ ይመለስ በሐዋርያት *ሥራ* ላይ ሃይለኛ ሕብረት የነበረው በቤት ውስጥ ነበር:: አብረው ይተጉ ፣ ይፀልዩ ፣ እንጀራን ይቆርሱ ነበር:: በበዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ መቶ ሃያ ዎቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልነበሩም ነገር ግን በአንድ ቤት ውስጥ ተሰብስበው ነበር በዚያም ቤት ውስጥ ሃይለኛ ፀሎት እተካሄደ ሳለ መንፈስ ቅዱስ እሳቱን ለቀቀ! እነጴጥሮስ እየተቀጣጠሉ ወጥተው ወን**ጌል**ን መስበክ ጀመሩ::

በቤታችሁ ውስጥ አምልኮ አለ ወይ? የዝማሬያችሁን ድምፅ ጌታ ኢየሱስ እየሰማ ነው? ዳዊት ምን አለ? *መዝ.2÷3 «እግዚአብሔር ሆይ በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ......»*ማለዳ ማለዳ ፊትህ ነኝ ማለቱ ነው ጠዋት ሲነሳ ጉዳዬ ከአንተ *ጋራ* ነው ማለቱ ነው:: በዓለም ውስጥ ብዙ ነገር ይፈልገናል ጊዜያችንንም የሚሻማ ነገር ብዙ ነው! ተማሪ ከሆንኩ ትምህርት ይፈልገኛል ሠራተኛ ከሆንኩ *ሥራዬ* ይፈልገኛል የእግዚአብሔር ቃል ግን «ለሁሉም ጊዜ አለው» ይለናል:: ትምህርት የራሱ ጊዜ ይኑረው ስራም የራሱ ጊዜ ይኑረው ከሁሉም በላይ ግን ለእግዚአብሔር ጊዜ አንጣለት:: «*በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ*» ትምህርት የሚቀርበት ዘመን ይመጣል! *ሥራም* የሚቀርበት ዘመን ይመጣል የሰው ነገር ሁሉ መቋጫ አለውና:: ብማርም እስከተወሰነ ጊዜ ነው ብሰራም እስከተወሰነ ጊዜ ነው! *ሥራዬን* ቢሆን ነገ እተዋለሁኝ! ትምህርቴም ቢሆን እንደዚሁ ይቀራል! ነገር ግን የዘላለምን አምላክ በምንም ነገር አትለውጡት! ዘለቄታ ያለውና የሚኖረው ነገር ምንድንነው ብንል ያም ለእግዚአብሔር የሰጠነው ነገር ብቻ ነው እግዚአብሔር ነገር ብቻ ነው! ዘላለማዊ ንብረታችን! ለእግዚአብሔር ዛሬ ጊዜዬን ፣ ገንዘቤን ብሰጠው ነገ ብድራት አለው::...

**ይቀጥላል...**